መስከረም ፲ ፪ሺ፪ (20-09-09) ዓመተ ምሕረት

መግቢያ

በሃይማኖት ጣልቃ ገቢዎች ኢትዮጵያውያን አይከፋፈሉም።

(መራ-ጌታ ገብረሥላሴ)
ቪሪታንያ

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤

እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም አሸጋገራችሁ ፥ ከ ፪ሺ፩ ወደ ፪ሺ፪ ዓመተ ምሕረትም በቸርነቱ እንኳን አደረሳችሁ!! አዲሱም ዓመት ለእናት ሀገር ኢትዮጵያ ሰላም ፤ ለቤክርስቲያን አንደነት ፤ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ላለነው **ኢትዮጵያውያን** ጤና ፤ ብልጽግና ፤ በረከት ፤ ጽናት ፤ የምናገኝበት ዘመን ይሆንልን ዘንድ የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን በማለት **ለኢትዮጵያውያን** ወገኖቼ የተሥዒነነ (በመስቀል) ፤ የሆያሆዬ ፤ የአበባዬ ሆይ ፤ ገጸ በረከት ትሆን ዘንድ ይችን ጸሑፍ በቅድስት ማርያም ስም አበረክታለሁ።

የዚች ጸሑፍ ምክንያት ፤ ባሁኑ ወቅት እናት ኢትዮጵያ በሁለቱ በትረ ስልጣኖቿ (ቤተ ክነት ቤተ መን ግሥት) የገጠማትን ታላቅ የፈተና ወቅት በመጠቀም ከውጭ በኩል በወዳጅነት ግልባብ (MASK)) በመሸፈን ፤ ሕዘቡን ለመከፋፈልና እርስ በርሱ እንዳይስማማ ለማድረግ የሚጠቀሙበትን የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ጣልቃ-ገብነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥንቃቄ እንዲመለከተው ፤ በተጠንቀቅ እን ዲጠብቀው ለመጠቆም ያህል ነው።

ለዚህም መነሻ የሆነኝ አሁን በቅርቡ በአሜሪካ ከንሳስ ስቴት የሚገኙ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ? ቤተ ክርስቲያን ምእመናን (August 15 2009; Quatero website) ያወጡት መግለጫ ነው። ምእመናኖቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ? ተከታዮች ነን ሲሉ ነገር ግን እናት ቤተክርስቲያን ስለ እመቤታችን ቅድስት ማርያም ለዘመናት የምታስተመረውን ወደጎን በመተው ፤ ለማንም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት **የባዕድ ልብ ወለድ አስተሳሰብ** በመያዝ ሕዝብን ለማሳሳትና ለመከፋፈል የሚያደርጉት ሩጫ ነው።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳዛኝ የሆነው መነሻቸው «..እመቤታችን ቅድስት ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት ፤ የአዳምን በደል ወርሳ ነው የተወለደችው ፤..» የሚል ሲሆን ይሄንንም ስሕተት ከነርሱ አልፎ ሌላውን ለማሳመን ደጋፊ ያገኙ መስሏቸው «...ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠይቀን መልስ ብናጣ ወደ ግብጽ ቤተክርስቲያን ጥያቄያችን አቅርበን አባ ሲኖዳ (የግብጽ ቤ/ክር መሪ) አጽድቀውልናል.....» ያሉት እጅግም የሚያሳዝና ከእውነት የራቀው ምክንያታቸው ነው።

ከዚህ ቀደም በመሪያቸው በቀሲስ አስተርአየ አዘጋጅነት ለቤተ ክህነት ባቀረቡትና በግንቦት ወር ፲፱፱፯ «በዜና ልደታ» (በአሜሪካ የሚዘጋጅ ጋዜጣ/መጽሔት) ላይ የወጣውን ጽሑፍ አስመልክቶ ጸሎታቸው አለየን በረከታቸው ይደርብንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቀውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ «ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ» በሚባል መጽሐፋቸው አምልተውና አራቅቀው መልስ ሰጥተዋቸዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤም ጽሑፉን አውግዘ ወድቅ አድርጎታል።

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጠይቀን መልስ ብናጣ ወደ ግብጽ ቤተክርስቲያን ጥያቄያችንን አቅርበን አባ ሲኖዳ (የግብጽ ቤ/ክር መሪ) አጽድቀውልናል.....» የሚለው አባባላቸው ጓደኛ ፍለጋ ቅልውጥ ሄዱ እንጂ ነገሩ እውነት ስላልሆነ በሕዝብ ዘንድ ትዝብት ላይ ከመውደቃቸው በስተቀር ማንንም ማታለል እንደማይችሉ ለሁሉም ግልጽ ነው።

ይሁንና በሌላ መልኩ ደግሞ ለነዚሁ ምእመናንም ሊታዘንላቸው የሚገባ ነው። ስለምን ? ቢባል በሣር ጎጆ ሆና እውነትን ከምታስምር ቤተ ክርስቲያን መጥተው አሜሪካ ፎቅ ላይ ሲቀመጡ የታቦር ተራራ

ሆኖላቸው አዲስ ሚስጢር የተገለጸላቸው ቢመስላቸውም ቅሉ እንኳንስ ይኼንን ረቂቅ ምስጢር ይቅርና ስለራሳቸው ፊደል አገባብ እንኳ አስተካክሎ የሚያስረዳቸው በዕወቀት የበሰለ ሰው በመካከላቸው ካለመኖሩና ከግላ ስህተት ገና ያልተላቀቁ ለመሆነቸው የተነሳ የደብራቸው ማኅተም በነርሱ ላይ ታማኝ ምሥክር ሆኖባቸዋል ።(August 15 2009; Qautero website) ያወጡት መግለጫ ይመለከቷል)

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ሲፈጥረው ክፉውንና በጎው መምረጥ የሚችል አእምሮ ሰጥቶ በነጻነት ስለፈጠረው **ግብጻውያንም የወደዱትን ማምለክና ማመን ይችላሉ ነገር ግን ትናንት እንደ ነበሩት ዛሬም ነገም በሃይማኖት ጣልቃ ገቢዎች ኢትዮጵያውያንን አይከፋፈሉም**። በዘያውም ላይ ምንም እንኳ **ወልደ ዋህድ** በሚለው መሠረተ እምነት አንድ ብንሆንም (ከጥንታውያን አባቶቻቸው ከነ አትናቴዎስ ቄርሎስ....) ተለይተው የአሁኖቹ የሃይማኖት ተወካዮች በሚፈላሰፉት በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ለንስማማ እንቻላለን። ለምሳሌም ያህል በምሥጢረ ሥላሴ ላይ አንስማማም ፤ ይሄንንም ወደፊት እን ደአስፈላጊነቱ ሊቀርብ ይችላል። በተጨመሪም እነርሱ እንኳ በአቅማቸው በእናት ኢትዮጵያ ላይ ሲያደርጉት የኖሩት ግፍና ቀልድ ፤ አሁንም ርስታችንን (ኢየሩሳሌም) ለመቀማት በአባቶቻችን ላይ የፈጸሙትንና እየፈጸሙ ያሉትን ግፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዘንጋት የለበትም።

የዛሬው ዋናው ነገራችን ግን ምን አልባት ከላይ የተጠቀሰው ስሕተት እውነት ሊሚሰለው የሚችል ወገን ሊኖር ስለሚችልና ሁኔታውንም በዝምታ ማየቱ ፤ ነገሩ ተቀባይነት ያለው እንዳይመስልና ስሕተት መሆኑን ለሕዝብ ማስገነዘብ የሃይማኖት ግዴታ ስለሆነ መልስ መስጠቱ አሰፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅድስት ድንግል **ማርያም** የምታምነውንና የሚታስተምረውን በየዘመኑና በየወቅቱ ፈጽሞ ያለተከለሰውና ቀጥተኛውን እምነት በጥቂቱ ለወገን ማቅረብም መልካም ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ማሳሰቢያ ለአንባቢያን ፤

የእምነት ጉዳይ ስለሆነ ጸሐፋን እውነትን ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ግእዙን ፤- **በደመቀ ጥቁር ቀይ** ፣ የግእዙን ትርጉም ፤- **በደማቅ ጥቁር** ስድ ነባቡን **በተለመደው** ሆኔታ በመጻፍ በተቻለኝ መጠን ቀለል ባለ አማርኛና ለሁሉም በሚመች አገላለጽ ለማቅረብ የሞከርኩ ሲሆን ፤ ነገር ግን **የፊደል ግድፈት ፤ የቃላት ስሕተት** ቢኖር እያረማችሁ በጥሞናና በህሊና ዳኝነት እንደታነቡት በትህትና አሳስባለሁ።

ጸሎት ፤ ዘለዓለማዊው አምላክ ፤ የንጉሦች ንጉሥ የገዢዎች ገዥ **ኢየሱስ ክስርቶስ** ሆይ ፤-

- በደምህ የዋጀሃት የቤተክርስቲያንህ ሰላም ይጠበቅ ዘንድ ፤
- በክቡር ደምህ የገዛሃቸው የምእመናኖችህ አንድነት ጸንቶ ይኖር ዘንድ።
- ከጌትነትህ ዙፋን ሳትለይ ዘጠኝ ወር በማኅፀኗ የተሸከመችህ የእናትህ የቅድስተ-ቅዱሳን የን ጽሕተ-ንጹሐን **ማርያም** የእናትነት ፍቅርዋ ፤ የምሕረት ቅልኪዳንዋ ሳየለየን እንኖር ዘንድ ፤

አሥግሩ ለነ ብለን ፍጡራንን ሳይሆን ፤ አንተ «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ **እግዚአብሔር** ትዘረጋለች..» ብልህ በአፈ ዳዊት እንደተናገርከው ፤

አሥግር ለነ ቁናጽለ ንዑሳነ
አለ ያማስኑ ዓፀደ ወይንነ መኃ ፪ ፥ ፲፭-፲፮ (2 ፥ 15-16)

ብለን እደ-ሊናችንን ሁልጊዜ ወደ አንተ እንዘረጋለን ፤ ስማን።
አሜን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ፮ዱ አምላክ አሜን

ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ አግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔር ሀገር ሆይ ስለ አንቺ የሚነገረዉ ልዩ ድንቅ ነው ። መዝ ፹፯ ቁ ፫ (80 ፥3) ግእዙን ተመልከት።

ነኪር የሚለው ቃል 1.ኛ **ነከረ**= **ለየ** **ነኪር** = **ልዩ** ከሌላዉ የተለየ የማይገናኝና በማንኛውም የማይመሳሰል 2.ኛ **ነከረ**= **ደነቀ** **ነኪር**= **ድንቅ** **የሚገርም** ለአእምሮ **የሚረቅ** ይህ ነው ተብሎ በልብ ትመርምሮ **ሊደረስበት** የማይችል ነገር ከሚለው የግእዝ ግሥ (Geez verb) የወጣ ቃል ነው። ።

እመቤታችን ከሰው ዘር የተገኘች ነገር ግን ከፍጥረት ሁሉ የተለየችና ድንቅ የሆነ ምሥጢር በእርሷ የተከናወና የእርሷም ነገር በሁሉ ዘንድ **ልዩና ድንቅ** ስለሆነ መንፈስቅዱስ በአፈ ዳዊት አስቀድሞ (ሳትወልድ) «ሰለእንቺ የሚነገረዉ የተለየ ድንቅ ነው» አለ። ንጽሕት ቅድስት ድንግል **ማርያም** በ**ልዩና** ለሰው ልቦና **ድንቅ** በሆነ ምሥጢር **በእናቷ ማሕፀን ከአዳም በደል ነጻ አድረጎ ፈጥሮ** ለእናትነት ስለ መረጣት በአምላክ ልቦና መታሰቧና ከልደቷ እስከ ዕረፍቷ ድረስ **በነቢያት ትንቢት በሐዋርያት ስብከት በሊቃውንት ትምህርት** የተነገረ እንጂ እንደ ውሃ ፈሳሽ እንደ እንግዳ ደራሽ ይደለም ። ይህንም በየረድፉ ይንመልከትዋለን።

የአዳም (የአለም) ደኅንነት ተስፋ ሁና መሰጠቷ እና ለአምላኳ እናት ትሆን ዘንድ መመረጧ

እግዝእትነ ማርያም ንበረት እምቅድመ ዓለም በሀሊና አምላክ ።

እመቤታችን ማርያም ዓለም ሳይፈጥር በአምላክ ህሊና ታስባ ትኖር ነበር። መቅ ዘዘወትር (ተአ ማር)

ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ያለ የሚኖር አምላክ ዓለሙን (Universe) ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ሲፈጥር በውስጡም የፈጠረውን ሁሉ እንደየፍጥረቱ አይነት በሚስማማው ቦታ ካስቀመጠ **በኋላ** ከፍጥረቱ አንዱ የሆነውን ሰው በገነት በተድላ በክብር አስቀመጠው ፤ በዚህ ዓለም ላለው ፍጥረት አዛኝ አደርገው። ነገር ግን የፈጣሪና የፍጡር የአዛኝና የታዛኝ ምልክት ትሆን ዘንድ የአንድ ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ አዘዘዉ። ኦሪ ዘፍ ፪፡ ፲፮-፲፯ (2 ፥ 16-18)

ከእርሱ አስቀድሞ የተፈጠረዉና በተሰጠው ያልጸና ለፈጠረው አልገዛም በማለት በትዕቢቱ የወደቀው (ሳጥናኤል) ዲያቢሎስ በቅናት ተነሳበት በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ ሐሰትን እውነት አስመስሎ (አሁንም ሰውን ሲያስት ብሌላ ተሠውሮ እንጂ ራሱን ገልጾ አይመጣም) ቆሮ ፲፩ ፲፭-፲፮ አዳምን አሳሳተው የፈጣሪውን ትእዛዝ አስፈረሰው ከፍጣሪው ጋር አጣላው። በዚህ ምክንያት አዳም ከርስቱ (ገነት) ተሰደደ ፤ ጸጋውን ተገፈፈ ፤ ልጅነቱን ተቀማ ፤ የሞት ሞት ተፈረደበት። ኦሪት ዘፍ ም 2 ና 3 ተመልከት። አዳም ግን «**ፈጣሪን ያህል ጌታ ፤ ገነት ያህል ቦታ አጣሁ**» ብሎ አዘነ አለቀሰ ። ጌታም እራሱን አስመስሎ በእጁ ስለፈጠረው አዘነለትና ከሞት ወደ ሕይወት ከስደት ወደ ርስት ከባዕድነት ወደ ልጅነት የሚመለስበት ተስፋ እንዲህ ሲል ሰጠው።

«..በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅክ ውስተ መርዓብከ ወእከውን ሕፃነ በእንቲአከ ወእትቤዘውከ በሞትየ ወበመስቀልየ ፤ **በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ-ልጅህ ተወልጀ ስለ አንተ ሕፃን ሁኜ በሜዳክ ድኜ ተሰቅየ ሙቼ አድንኃለሁ..»** አክሲማሮስ ዘዓ።

ዳግመኛም ከዚችም የአዳም የልጅ ልጅ ከተባልች የአዳም መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ቅድስት ድን ግል ማርያም በኋለኛው ዘመን ተወልዶ እንደሚያድነውና የአዳምም ሥጋ በተዋሕዶ አምላክ እንደሚሆን

«..*ወአምይእዜ ኮነ አዳም ከመ አሀዱ እምኔነ* ከእንግዲህ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ..» ኦሪ ዘፍ ፫፡ ፳፪ (3 ፡22) በማለት ገልጸለት።
ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አዳም የሚድንበትን ተስፋ አወቀ ፤ የተስፋውም መፈጸሚያ ማን እንደምትሆን ተረዳ ከራሱ ሥጋ የምትገኝ እንድሆነች ቀን ቀጠሮው እስከሚደረስ ድርስ በዚህ ተስፋ ቆየ። ለዚህ ነው አባ ሕርያቆስ ፤ «*አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት* ፤ ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ» ሲል ያመሰገናት ቅዳ ማር

ውድ ወገኖቼ ፤-

1. እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው አዳም ኃጥአት ሠርቶ ካገኘው መከራ ነጻ ሊወጣባት ተስፋ ሆና ድንግል ተሰጠችው እንጂ ንጽሕት ድንግል ማርያም የአዳም ኃጥአት ተካፋይ እንድትሆን አለመሆኑን ግልጽ አድርጎ ነው የሚነግረን የእግዚአብሔር ቃል ።

2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተነገረው እመቤታችን ድንግል ማርያም የአዳም ልጅ (የሰው ዘር) መሆኗን ታምናለች ታስተምራለች እንጂ እንደሌሎች ከሰማይ የወረደች ኃይል ናት አትልም ፤ እንደዚህ የሚሉትንም ታወግዛለች።

የድንግል ትውልድ በነቢያት ፤ በሐዋርያት ፤ በሊቃውንት ፤

በአባቷ በኢያቄም በኩል ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አንዱ ከሆነው ይሁዳ በኩል የንጉሥ ዳዊት ዘር ናት (ቤተ መንግሥት) በእናቷ በኩል አሁንም የያዕቆብ ልጆች አንዱ ከሆነው ከሆነው ከሌዊ ዘር ከካህኑ አሮን ናት (ቤተ ክህነት) ሉቃ ፩፡፳፬ (3 ፣ 24) መቅ ተአ ዘዘወትር

«..ትወጽእ በትር እምሥረወ እሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምኔሃ ፤ ከእሴይ ሥር (ወገን) በትር (ድንግል) ትወጣለች ከእርሷም አብባ (ጌታ) ይገኛል (ይወለዳል)..» ኢሳ ፲፩፡ ፩ (11 ፣ 1)በማለት ከእርሷም የሚወለደዉ ጽጌ ክርስቶስ ማን እንደሆነ እና ለምን እንደሚወለድ ነቢዩ ያስተምረናል።

ቅዱስ ጳውሎስም ያብርሃም ዘር መሆኗን ሲገልጽ እንዲህ አለ ፤*«....አስመ አኮ አመላእክት ዘነሥአ ለዘነስኦ ዘእንበለ ዳዕሙ አምዘርኣ አብርሃም ፤* የነሳውን (ሥጋ) ከመላእክት የነሳው አይደለም ከአብርሃም ዘር ነው እንጂ..» ዕብ ፪፡ ፲፮፻፮ (2 ፡ 16-17) ሊቃውንትም በዚሁ ተባብረውበታል።

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ «...*ወአስተርአየ እምሥርወ እሴይ ወዳዊት በሥጋ አስመ እምኔሆሙ ተወልደት ድን ግል ማርያም ንጽሕት ፤* ከእሴይና ከዳዊት ባህርይ በሥጋ ተወልዶ ተገለጠ ፤ አምላክን የወለደች ን ጽሕት ድንግል ማርያም ከእነርሱ ተወልዳለችና..*»* ሃይ አበ ፹፮፡ ፫ ሲል

ኤፍሬም ሶሪያዊ ፤ *አንቲ ውእቱ ዘመድ ዘእምሥርወ ዳዊት ፤* ከዳዊት ዘር የተገኘሽ ዘመድ አንቺ ነሽ የማክ ውዳ.ማ.ቅ. በማለት ያደላድላል ፤

ቅዱስ *ያሬድ*ም «...*እምሥርወ እሴይ ሠሪፃ ወእምኵንደ ዳዊት ተወሊዳ ተዓብዮ ነፍስየ ትቤ ድንግል ሳይዳ* ፤ ከእሴይ ሥር ተገኝታ ከዳዊትም ዘር ተወልዳ ፤ ብላቴናዋ ድንግል ነፍሴ (እግዚአብሔርን) ከፍ ከፍ ታደርገዋለች አለች....» ዝማሬ ዘልደታ በማለት ምስጢርን ይጋራል።

ከአዳም በደል ነጻ ሁና መወለዷና የተወለደችበት ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ።

«.....በጽሐ ሠናይ ወአልጸቀ ዘመን ወበዓለ ለቅድስት ማርያም ፤ መልካም ነገር ደረሰ ፤- ዘመኑም ተቃረበ ቅድስት ማርያም የምተመሰገንበት ደረሰ..» ቅ/ያሬድ ድጓ ዘነሐ ኪዳ ምሕ። መኃ ፪፡ ፲፪፻፪

የመከራ ዘመን አልቆ የድኅነት ዘመን ሲቀርብ 16 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነሐሴ 7 የአምላክ እናት ቅድስት ማርያም ተፀነሰች። በእናቷ ማሕፀን እያለች ድንቅ ድንቅ ታምራት (ሙት እስከ ማስነሳት) እየሠራች ሲያዩ የገዛ ዘመዶቿ ቤተ እስራኤል ቀንተው «እናቲቱን ሐናን በደንጋይ ወግረን ከነጽንሡ እንግደላት» ብለው ሲመክሩ የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄምና ሐና ወደ ሊባኖስ (Lebenon) ዱር

እንዲሸሹ ነገራቸውና በዚያ ግንቦት ፩ ፭ሺ፬፻፹፯ (15 ዓመት ከከርስቶስ ልደት በፊት) ተወለደች። ይሄም የሆነበት ምክንያት ፤-

ኩለንታኪ ሠናይት እንተ ኀቤየ ፤ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ ፤ ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ።

<u>በእኔ ዘንድ</u> ኹለንተናሽ ያማረ ነው (ውብ ነሽ) ፤ <u>ባንቺም ምንም ነውር የለብሽም</u> ፤ <u>ከሊባኖስ ነዪ ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ነዪ።</u> መኃ ፬፡ ፯ (4 ፥ 7-8) ተብሎ የተነገረለት ይፈጸም ዘንድ ነው። የተወደደዳችሁ ክርስቲያኖች ሆይ ፤- ይህን ቃለ ትንቢት ስለ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ገናና ክብር አጉልቶ ያስረዳናል። ይኼንኑንም በሦስት ክፍል እንመለከተዋለን።

<u>ክፍል አንድ</u>

ኩለንታኪ ሠናይት እንተ ኀቤየ

<u>በእኔ ዘንድ</u> ኹለንተናሽ ያማረ ነው (ውብ ነሽ) ፤

<u>1.ኛ በእኔ ዘንድ ፤-</u> በእርሱ በሕያው አምላክ ዘንድ ፍጡር ስትሆን ነገር ግን ከፍጡራን ተለይታ ለእርሱ እናትነት ስለመረጣት ፤ **<u>ኹለንተናሽ ፤-</u>** በውስጥ በአፍአ ንጽሐ ጠባይ ያለደፈበሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ (የአዳም በደል) የሌለብሽ..... **<u>ውብ ነሽ</u>** ፍጽምት ቅድስት ንጽሕት ነሽ ሲል እንዲህ አለ።

<u>2.ኛ በእኔ ዘንድ</u> አለ እንጂ በሌሎች ዘንድ አላለም። በሌሎች (በሰዎች) ዘንድ አምሮ ተውቦ መገኘት የአፍአ (ሥጋ) ነው ፤ በአምላክ ዘንድ አምሮ ተውቦ መገኘት ግን (የውስጥ) ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ መገኘት ነውና።.....?

<u>ኹለንተናሽ ፤-</u> የሚለው ቃል ደግሞ ፈጹም ሰውነቷን ፤ ነፍስና ሥጋዋን ፤ ስነ ጠባይዋንና ግብሯን የሚገለጽ እንጂ በከፊል እንዳልሆነ ያስረዳል። **<u>ውብ ነሽ.....</u>** በዚህ ሁሉ ፍጽምት ቅድስት ንጽሕት ነሽ አለ።

<u>ክፍል ሁለት</u>

አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ

<u>ባንቺም ምንም ነውር የለብሽም</u> ፤- <u>ምንም ፤-</u> የሚለው ቃል የሌለ ፤ ያለቀ ፤ ባዶ ፤ ቀሪ የሌለው.....የመሰለውን ሁሉ ይገልጻል። **<u>ነውር</u>** የሚለው ቃል ደግሞ ኃጢአት ፤ በደል ፤ ጉድለት ፤ አደፍ ፤ ጉድፍ ፤ ጸያፍ.....ተብሎ ይተረጎማል።

የተወደደዳችሁ ክርስቲያኖች ፤- አያችሁት የእግዚአብሔርን ቃል ወደፊት ከእርስዋ የሚለደውን ክርስቶስ **<u>ዘአልቦ ነውር ፤-</u>** ነውር የሌለበት እንዲለው ዕብ ፱፡፲፬ (9 ፥14-15) እርስዋንም ገና ሳትወለድ **<u>ባንቺም ምንም ነውር የለብሽም</u>** ብሎ በነፍስ በሥጋዋ ፣ በውስጥ በአፍአ ንጽሕት ቅድስት የሆነች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ (የአዳም በደል) የሌለባት መሆኗን በትንቢት እንዲህ አድርጎ ገለጸ ሲነግረን!!

<u>ክፍል ሦስት</u>

ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ።

<u>ከሊባኖስ ነዪ ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ነዪ።</u> የአብ ሙሽራ የወልድ ማደሪያ የመንፈስቅዱስ ታቦት የሆነችው ድንግል ስለማንነቷ ይቅርና በየት ቦታ እንደምትወለድ እንኳ የእግዚአብሔር ቃል በገልጽ ይናገራል። **<u>እምሰሚዕ ይኄይስ ርእይ</u>** ከመስማት ማየት ይበልጣል ይላልና እግር ያደረሳችሁ ወገኖች ሊባኖስን በምትጎበኙበት ጊዜ ድንግል የተወለደችበትን ቦታ መጎብኘቱ መልካም ነው። አለበለዚያም ከቤታችሁ ሁናችሁ በጉግል-ኧርዝ (GOOGLE EARTH) ማሠሥ ትችላላችሁ። **<u>ታዲያ የዘመናችን ተፈላሰፊዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተላልፈው በራሳቸው መላ-ምት አስተሳሰብ ምእመናንን ለማደናገር መሞከራቸው ምን ሊጠቀሙበት ይሆን?</u>** ትዝብቱን ለአንባቢያን እተዋለሁ።

ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ

እበውእ ቤተከ ምስለ መባዕየ ፤ ወእሁብ በጽዐትየ ዘነበብኩ በአፋየ ፤ ዘእቤ አመ ምንዳቤየ።
ከመባእየ ጋር ውደ ቤትህ እገባለሁ ፤ በችግሬ ጊዜ ያልኩትን በአፌ የተናገርኩትንም ስለት እሰጣለሁ።
መዝ ፷፮፡፲፫፲፭ (65 ፥14-15) ተብሎ በተነገረው ትንቢት መሠረት ድንግል ማርያምን አናትና አባቷ ለእግዚአብሔር ተስለው ስለወለዷት ፤ በተወለደች በሦስት ዓመቷ ለቤተ እግዚአብሔር ስጦታ አድረገው አስረከቧት። በዚያም አባ ሕርያቆስ «ድንግል ሆይ ምድራዊ ምግብን የተመገብሽ አይደለም ከሰማየ ሰማያት የተገኘ ነው እንጂ ፤ ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ አይደለም ከሰማየ ሰማያት የተቀዳ ነው እንጂ...» ቅዳ ማር ፤ ብሎ እንደተናገረ ፲፪ (12) ዓመት ሙሉ በመልአኩ ፋኑኤል አቀራቢነት ሰማያዊ ምግብ እየተመገበች ሰማያዊ መጠጥ እየጠጣች ኑራለች።

ወገኖች ሆይ ከባድና ረቂቅ ምሥጢር አለና በአንክሮ ተመልከቱት። ይሄውም ፲፪ (12) ዓመት ሙሉ **ኑሮ** በቤተ **እግዚአብሔር** ፤ **ምግብና መጠጥ** ከሰማይ ፤ **አቅራቢ** አሳታዊ ምልአክ ፤ **ጎብኚችና አጫዋቾች** አሳታውያን መላእክት ፤ (ከእርሷ ሰነ ፍጥረት የተለዩ) በዚያውስ ላይ **ምን ምስጢር** እየተነገራት **ምን ሥውር ነገር** እየገለጸላት እንደኖረች በእርሷና በፈጣሪዋ መካከል የሆነ ረቂቅ ምሥጢር ሲሆን ከሰው ልጆች ግን የተሠወረ ነው።

እንደዚህ ያለው ነገር ሰውነቱ በአዳም በደል ለተተበተበ ሰው ይሆናልን? ኧረ አባከችሁ አናስተውል ወገኖቼ። ለዚህም ነው እኮ ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር ፤- ስለአንቺ የሚነገረው የተለየ ነው የሚለው። አባ ኤፍሬምም አይ ልሳን ዘይክል ነቢበ ዘይትነገር በእንቲአኪ አ ድንግል ንጽሕት ድን ግል ንጽህት ሆይ ስለአንቺ የሚነገረውን አከናውኖ ሊናገር የሚችል ምን አንደበት ነው ፤ የማክ ውዳ ማር። ብሎ የተናገረው።

መንግሥቱ በእርስዋ በኩል እንዲፈርስበት ያወቀ ዲያብሎስ ከፅንሰቷ ጀምሮ-እሰከ ዕረፍትዋ ድረስ እርስዋን ለማጥፋት በልበ አይሁድ እያደረ (አሁንም ማደሪያ አለጣም) በእርስዋ ላይ ያነሳሳቸው ጀመር። ሦስት ዓመት በእናት አባትዋ ቤት ፤ ፲፪ (12) ዓመት ሙሉ በቤተ እግዚአብሔር ፤ ድምር አሥራ አምስት ሲሞላት «እቅመ ሔዋን ስላደረሰች ከቤተ መቅደሳችን ተውጣልን» እያሉ ስለተነሳሱበት ጥንቱን ለእናትነት የመረጣት አምላክ በልዩ ምልክት ባጎቷ ልጅ በዮሴፍ እንድትጠበቅ አደረገ። እን ግዲህ በዮሴፍ ቤት ሳለች ነው ጌታን የጸነሰች። ማቴ ፩ ፡፲፰-ፍጻሜ (1 ፥18-ፍጻሜ)

ልዩ ትኩረት አሁን ፤

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ደም የተዋጃችሁ የንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም የቃልኪዳኗ ልጆች ሆይ ዋና የተነሳነበት ጥንተ ነገር ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም በደል ሳይተላለፍባት ተወልዳ አምላክችንን ወለደች ነውና ፤ በግምት ወይም በይሆናል ሳይሆን የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን መልእክትና ምስክርነት እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ያስመሰከራቸውን የቅዱሳን አባቶች ትምህርት ይዛ ነውና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረችሁ የሚከተለውን ቁም ነገር ልዩ ትኩረት ሰጥታችሁ እንድትከታተሉ አሳስባለሁ።

የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን መልእክትና ምሥክርነት

ወበሳድስ ወርኅ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አሀቲ ሀገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ኀበ ድንግል እንተ ተፍኅረት ለበአሲ ዘስሙ ዮሴፍ ዘእምቤተ ዳዊት ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም.....እስከ ኀበ ይብል ወሐለፈ መልአክ እምኔሃ። ሉቃ ፩ ፳፮-፴፰ (1 ፥ 26-38)

(የዮሐንስን ልደት ለዘካርያስ በነገረው) በስደስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሚሆን ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ ፥ የድንግሊቱ ስምም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደእርስዋ ገብቶ ፤ ደስ

ይበልሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ፤ አንቺም ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ።

ለተነሳነበት ነጥብ ድንግል ከአዳም በደል ለጸ ለመሆንዋ ምሥክር ይሆነን ዘንድ በሁለት ከፍለን እንመለከተዋለን።

1.ኛ የድንግል ማርያምን ክብር የሚገለጽ የቅዱስ ገበርኤል ሰላምታ ፤-

ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም የተላከው ፤ አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልድ ዘንድ ይነግራት ነው እንጂ ስለ ኃጢአት መንጻት ጉዳይ ፈጽሞ እንደይደለ ለሁሉም ግልጽ ነው። ይሄም ሲሆን መልአኩ መልእክቱን ከዚህ ቀደም ለሌሎች ተደረጎ በሚያውቅ ምስጋናና ሰላምታ ነው የጀመረው። አለፍ አለፍ ብለን እንኳ ቃላቶችን ብንመረምር ሌሎች እንደሚሉት ሳይሆን የድንግልን ገናና ክብር ፤ ቅድስናዋንና ንጽሕናዋን እንዲሁም መመረጥዋን ነው የሚያሰረዳው።

ደስ ይበልሽ ፤- ጥንቱን የተመረጠችበት የአዳም (የዓለሙ) ደኅንት ሊፈጸም ነውና ፤ ርኅርኅተ ልብ ስለሆነች እርስዋ የምታዝንለት በኃጢአት የተጎዳው አለም ነጻ ሊወጣ ነውና ፤ በዚያውም ላይ የአምላክ እናት መሆን ከሁሉ በላይ እጅግ ደስ ያሰኛልና።

ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ፤- ጸጋ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ይተረጐማል ፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚያደርገውና የሚሰጠው ሀብት ሁሉ ልጅነትንና ድኅንትን ጨምሮ ጸጋ በሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ ይገለጻል። ዮሐ ፩፡፲፮-፲፰ (1 ፡16-18)። ሮሜ ፲፪፡፮ (12 ፡ 6)። ኤፌ ፫፡ ፯-፰ (3 ፡ 7-8)።

ለእመቤታችን ግን ለፍጡራን ከቶ ሊሰጥ የማይችል ጸጋ ተሰጣት። ለምሳሌም ያህል ለዓለም የድኅንት ቃልኪዳን መሆን ፤ በማሕፀነ እም ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ (ከአዳም በደል) ነጻ መሆን ፤ ዘለዓለማዊ ድንግልና ፤ ከሁሉም በላይ አምላክን መውለድ.....የመሰለውን ሁሉ (ወደፊት እን መለከተዋለን) ጸጋ አስቀድሞ ስለተሰጣት መልአኩ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ብሎ በኃላፊ ዓረፍተ ነገር (past tense) የተናገረው። ከብሥራት በኋላ ነው የነጻች (ሰአሊ ለነ ቅድስት) ብለው ተጠራጣሪዎቹ እን ደሚሉት ቢሆን ኑሮ ቅዱስ ገብርኤል ጸጋን የምትሞይ ብሎ በመጻዒ ዓረፍተ ነገር (future tense) በተናገረ ነበር።

እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ፤- ለሰው ልጅ የድኅንት ቃልኪዳን ሁና የተሰጠች በመሆንዋ እግዚአብሔር ስለእርስዋ በቅዱሳን ነቢያቶቹ አድሮ ያለነገረበት ጊዜ የለም። በዚያውም ላይ እርሱ ቅሉ ገና ሳትወለድ አስቀድሞ ለእናትነት የመረጣት ስለሆነች እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው አለ መልአኩ። ስለዚህም ነው መንፈስቅዱስ በአፈ ዳዊት ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል.....ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ ፤ (ቀደሰ=አነጻ ከአዳም በደል ፤ ቀደሰ=አከበረ ከፍጥረቱ ሁሉ ፤ ቀደሰ=ለየ ከዓለም ሴቶች) እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም ብሎ የተናገረ። መዝ ፵፮ ፬-፭ (45 ፡4-5)

ከሴቶች መካከል አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤- ከእርስዋ በፊትና በእርስዋ ጊዜ ከነበሩት ከእርስዋም በኋላ ከሚመጡ ሴቶች እንደ እርስዋ ያለ ስላልተገኘ እርስዋ ብቻ ገረዱ ስትሆን እናቱ ልትሆን ፤ ፈጣሪዋ ሲሆን ልጅዋ ሊሆን የተመረጠች መሆንዋን መልአኩ እንዲህ አለ። ከሴቶችም ልዩ የሚያደርጋት ፤

- ሴቶች በአዳም በደል ምክንያት ንጽሐ ጠባይዕ ስላደፈባቸው በገቢር (አድራጎት) ቢነጹ በሀሳባቸው አይነጹም እርስዋ ግን ንጽሐ ጠባይዕ ስላላደፈባት በገቢርም በሀሳብም ንጽሕት ናትና ፤
- ሴቶች የሚወልዱት በተፈትሦ ማሕፀን ፤ ሲሆን እርስዋ ግን ሳትፀንስ ፤ በፀነሰችም ጊዜ ፤ ከፀነሰችም በኋላ ፤ ሳትወልድ ፤ በወለደችም ጊዜ ፤ ከወለደችም በኋላ ድንግል ናትና። ሕዝ ፵፬ ፡ ፪-፫ (44 ፡2-3)
- በሴቶች ላይ በአሪቱ መርገመ ሔዋን ተብሎ የሚታወቀው ወርኃዊ ግዳጅ ፤ በምጥ በጭንቅ መውለድ ሲኖር በእርስዋ የለምና። የአዳም በደል (ጥንተ አብሶ) የለባትም

የሚያሰኘው አንዱ ይህ ነው። ከሰው ዘር ተለይታ ከአዳም በደል ነጻ ባትሆን ኑሮ በጸታ አንስት ከሴቶች ተለይታ ከሔዋን መርገም ነጻ ባለሆነችም ነበር።

- ሴቶቸ በዘር በሩካቤ ዕሩቅ በእሲን ሲወልዱ እርስዋ ግን ያለዘር ያለሩካቤ ፈጣሪዋን ነውና የወለደቸው።

ከብዙ በጥቂቱ በተዘረዘሩት ምክንያት ስትፈጠር እመቤታችን ከጥንተ አብሶ ነጻ መሆንዋን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በኃላፊ ዓረፍተ ነገር (past tense) ከሴቶች መካከል አንቺ የተባረክሽ ነሽ ሲል ፤- እንደገና «በሁለት በሦስት ምሥክርንት ነገር ይጸናል» እንደተባለ ማቴ 18 16-17 መንፈስቅዱስ መልሶ በቅድስት ኤልሳቤጥ ላይ አድሮ የመልአኩን ምሥክርነት ለማጽናት ደገመው።«.....በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞለባት ፤ በታላቅ ድምጽም ጩኻ እንዲህ አለች «....ከሴቶች መካከል አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንሽ ፍሬም የተባረከ ነው የጌታዬ እናቱ ወደእኔ ትመጣ ዘንድ እን ዴት ይሆናል.....»ሉቃ ፩፡ ፵፪ ፵፬ (1 ፡ 42-44) የሚገርመው እናቱን የተባረክሽ ነሽ ብላ ያከበረችበትን ፤ ልጅዋንንም የተባረከ ነው ብላ አጋራቻቸው።

2.ኛ ቅ/ገብርኤል ከተፈጠረች ጀምሮ ከጥንተ አብሶ ነጻ መሆናዋን ለድንግል ሲመሠክር ፤

መልአኩ ከላይ በተመለከትነው ሁኔታ ያለተለመደ ሰላምታ ቢያቀርብላት ከአነጋገሩ የተነሳ ደነገጠችና «እንዴት እንዲህ ያለ ሰላምታ ይቀበሏል?» ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት ፡ ማርያም ሆይ አትፍሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግንተሻልና እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ተወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ፡ እርሱ ታላቅ ነው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ለያዕቆብ ቤትም ለዘለዓለሙ ነግሦ ይኖራል ለመን ግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

አንብቢው ያሰተውል

ማርያም ሆይ አትፍሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግንተሻልና ፤-

ከመፈጠርዋ በፊት ገና ለእናትነት ስትታሰብ ጀምሮ ስለሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን ያገኘች ፤ መልአኩ አግኝተሻልና አለ እንጂ ታገኛለሽ አላለም። ባለሟልነት ማለትም መወደድ ፤ መፈቀር ፤ የቅርብ ተጠሪ ፤ ታማኝ መሆን ፤ መሾም ፤ መከበር...ማለት ነው።

እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ተወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ብሎ ስሙን

እርሱ ታላቅ ነው ብሎ አምላክነቱን ፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል ብሎ ሰማያዊ አባት እንጂ ምድራዊ አባት አለመኖሩን ፤ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ብሎ በእርስዋ ምድራዊት እናቱ በኩል ከዳዊት ዘር መወለዱን ፤ ለያዕቆብ ቤትም ለዘለዓለሙ ነግሦ ይኖራል ብሎ በእርስዋ በኩል ከቤተ እስራኤል ዘሥጋ መወለዱን በምሥጢር ግን እስራኤል ዘነፍስ (ክርስቲያኖች) ንጉሥነ ወአምላክነ ማለታቸውን ፤- ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም። ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን ነገራት

አንብቢው ያሰተውል

ማርያምም ፤ መልአኩን «ወንድ ሳለውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?..» አለችው።

ወገኖቼ ሆይ የድንግልን ጥያቄ ልብ ብላችሁ አስተውሉ። በድንግልና ፀንሶ በድንግልና መውለድ በሰው ዘንድ ያልተለመደ ስምታውና ዓይታው የማታውቅ አዲስ ነገረ ስለሆነ ፤ «..ወንድ ሳለውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል ?..» አለችው እንጂ ፤ ሌሎች ጌታን ከመፅነሰዋ በፊት (ደፋሮች) ጥንተ አብሶ ነበረባት ብለው መለ-ምት እንደሚናገሩት ቢሆንማ ኑሮ ድንግል (እመቤቴ ይቅር በይኝ ስለ አንቺ አውነት ለመመሥከር ነውና) እኔ በደለኛ ስሆን እንዴት አድርጌ አምላክን ያህል እወልዳለሁ ባለችው ነበር ገና አልፀነሰችምና።

መልአኩም መልሱ እንዲህ አላት የቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ(ቅዱስ) ባንቺ ላይ ይመጣል (ያድርብሻል) ፤ የልዑል (አብ) ኃይልም ይጸልልሻል (ይጋርድሻል) ፤ ካንቺ የሚወለደውም ቅዱስ (ወልድ) ነው ፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል ፤ እነሆ ከዘመዶችሽ ወገኖች የምትሆን ኤልሳቤጥ እርስዋ

በእርጅናዋ ወራት ፀነሰች ወንድ ልጅም አገኘች መኻን ለሚሏትም እነሆ ይህ ስድስተኛ ወሯ ነው ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለምን ድንግል ማርያም ከአዳም በደል ንጽሕት ናት እን ደምትል እናስተውል።

መልአኩ ድንግል ላቀረበችልት ጥያቄ በሰው ልቡና ሊሚረመርና ሊታሰብ የማይቻለውን ረቂቅ የተዋሕዶን ምሥጢር በእርስዋ ላይ እንዴት እንደሚከናወን ገለጸላት እንጂ ለተጠራጣሪዎች መላ-ምት ሀሳብ በር አልከፈተም። ከገለጸላትም አንዱ የልዑል (አብ) ኃይልም ይጸልልሻል (ይጋርድሻል) የሚለውን እንመልከት። ይጸልልሻል (ይጋርድሻል) የሚለው ቃል ጸለለ (አጥብቆ)=ጋረደ ፤ ከለለ ፤ ሸፈነ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ነው። መጋረደም ከውስጥ ያለን ከቡር ነገር ከውጭ ከሚመጣ የማይፈለግ ነገር መጠበቅ ማለት ነው።

ጥንቱን ለእናትነት የመረጣት ከማሕፀነ ሐና ጀምሮ ከውርስ ኃጢአት የጠበቃት ፤ በውስጥ በአፍአ ያነጻትና ያከበራትን ቅድስትና ንጽሕት የሆነችውን ፲፭ ዓመት ብላቴና ከሥጋዊ አፍአ (በስተውጭ) ከሚመጡ ሩካቤ ፣ ዘር ፣ የድንግልና መለወጥ ተብለው በሰው ዘንድ ከተሠሩትና ከታወቁት ሦስት ግብራት (ስራዎች) ይከልላት ይጋርዳት ዘንድ ስለሆነ መልአኩ የልዑል (አብ) ኃይልም ይጸልልሻል (ይጋርድሻል) አለ። ይኸንንም የአስክድርያው (ግብጽ) ሊቀጳጳስ ስንትዩ እንዲህ ሲል ይተረጉመዋል።

«..ወውእቱ ይእዜ ንጹሕ እምፎቱ ግብራት እለ ሥሩዐት በዕንለ እመሕያው ወእሙራት ቦሙ ዘውእቶሙ ሩካቤ ወዘርእ ወሰስሎተ ድንግልና እንዘ ይሜህረነ በዘንቱ ቡሩክ ወልዑል ከመ አልቦ ዘይትማሰሎ ለልደቱ አምኩሎሙ ዕንለ እመሕያው ወበውስተ ኩሉ እንስሳ ኢኮነ እምቅድመዝ ወኢይከውን እምድኅረዝ ወበእንተ ዝንቱ ጠየቅነ ከመ ድንግል ይእቲ ወላዲተ አግዚአብሔር ቃል።

አሁንም እርሱ በሰው ዘንድ ከተሠሩ ከታወቁ ከሦስቱ ግብራት ንጹሕ ነው። እነዚህም ሩካቤ ፣ ዘር ፣ የድንግልና መለወጥ ናቸው ፤ ቡሩክ የባሕሪ አምላክ እርሱ ከሰው ከእንስሳ ልደቱን የሚመስለው እን ደሌለ በዚህ ሲያስረዳን በድንግልና መወለድ ከዚህ በፊት አልተደረገም ከእንግዲህም አይደረግም ፤ ስለዚህም ድንግል እግዚአብሔር ቃልን የወለደች እንደሆነች ተረዳን...»። ሃይ አበ ፻፲፡ ፳፱ (110 ፡ 29)

<u>አንባቢው ያስተውል ፤-</u> ሌሎች እንደሚሉት ድንግል የውርስ ኃጢት ቢኖርባት ኖሮ መልአኩ የልዑል (አብ) ኃይልም <u>ይጸልልሻል</u> (ይጋርድሻል) በማለት ፋንታ <u>ያነጻሻል</u> ባለ ነበር። በነፍስና ሥጋ ለተቆራኘ ኃጢአት ተስማሚው ቃል መንጻት ነውና። አብ ፱፡ ፲፱፻፳፭ (9 ፡ 15-15) ወንጌላዊው ዮሐንስም «<u>ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሀነ አምኩሉ ኃጣውኢን</u> የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም ከኃጢአታችን <u>ያነጻናል</u>» ሲል ቃሉን ለይቶ ይናገራል 1.ኛ ዮሐ ፩ ፡ ፯ (1 ፡7-8)

ማርያምም መልአኩን «..እንሆ የእግዚአብሔር ገረዱ እለሁ እንዳልክ ይሁንልኝ..» አለቸው። ከዚህ በኋላ መልአኩ ከእርስዋ አልፎ ሄደ። ሉቃ ፩፡ ፳፯፻፴፱ (1 ፡ 26-39)

የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች ፤- ከዚህ ላይ በግልጽ እንደተረዳነው ወንጌላዊው ሉቃስ ያልጻፈውን ፤ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ያልተናገረውን ፤ ንጽሕተ ነጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ያላለችውን በምንም አይነት ፤ በእርእስት ፤ በምሥጢር ፤ በአንቀጽ ፤ በቋንቋ የማይገናኘውን ከመጽሐፍም ያልተገኘውን በልብ ወለድ ሀሳብ ብቻ በመነሳት «መልአኩ በአበሠራት ጊዜ ከአዳም በደል ነጻች» ብሎ በኃያሉ እግዚአብሔር እናት ላይ በድፍረት መናገር ፤ ሌላውንም ለማደናገር መሞከር ለምን የሆን? እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው አይቁጠርባቸው።

<u>የሊቃውንት ምስክርነት ፤-</u>

ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ንጽሕና ቅድስና ልዕልናና ክብር ብቻ በነቢያት ብቻ በሐዋርያት ብቻ በመልአኩ ብቻ በኤልሳቤጥ ተነግሮ የቀረ አይደለም። በሐዋርያት እግር ተተክተው (አዕማደ ቤተክርስቲያን) ለቤተክርስቲያን ዐምድና መሶሶ የሆኑት ሊቃውንት መንፈስቅዱስ እንደገለጸላቸው መጠን

ስለድንግል ከውርስ ኃጢአት ነጻ ለመሆንዋና መሥክረዋል አስተምረዋል። ዛሬም የክብር እንግዶች አድረገን ለምሥክርነት እናቀርባቸዋለን

በነቢያት የተነገረው (ኢሳ ፪፡ ፲፬) ይፈጸም ዘንድ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አብሣሪነት በማይመረመር ምሥጢር በግብረ መንፈስቅዱስ አካላዊው ቃልን በማሐፀንዋ ፀንሳ መገኘትዋ በዮሴፍ ዘንድ ከባድ እንደ ነበር ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ ተረኮልናል ማቴ ፩፡ ፲፰ኽፍ (1 ፥ 18-ፍ) ይሄንን እን ቀጽ በተረጐመበት ክፍል የቀስጥንጥያው ሊቀ ጳጳስ ኤራቅሊስ እንዲህ ይላል።

ኢያእመረ (ዮሴፍ) አስመ ዘተፈጥረት እምነ ጽቡር ጽኑይ ትከውን መቅደሱ ለእግዚአብሔር ፤ ኢያእመረ አስመ ዘለዓለም እንበለ ርኵስ አዳም ዳግማዊ ይትፈጠር ውስተ ገነት ድንግልናዊት።

ከንጹሕ አፈር (ዘር) የተፈጠረች ድንግል የእግዚአብሔር ማደርያ እንድትሆን አላወቀም መለወጥ የሌለበት ዳግማይ አዳም ክርስቶስ ድንግልና ካላት ገነት እመቤታችን እንዲገኝ አላወቀም። ሃይ አበ ፵፰፡ ፴፩ (48 ፥ 31)

በእርግጥ ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም በስተቀር ከአፈር የተፈጠረ የለም ከዚያ በኋላ ግን በዘር በሩካቤ ነው ፤ ደንግልም በዘር በሩካቤ የተወለደች ስትሆን ነገር ግን በዚህ ምክንያት የሚተላለፈው የውርስ ኃጢአት በማሕፀነ ሐና ወደእርስዋ እንዳልተላለፈና ካዳም በደል ነጻ ሁና ተወልዳ ጌታን እን ደፀነሰች ሲያስረዳ ይህ አባት ኤራቅሊስ «..ከንጹሕ አፈር የተፈጠረች ድንግል.....». አለ። የትውልድ ክብር ቢሆን ኖሮ የተወለደች ባለ ነበር ነገር ግን የስነ ተፈጥሮ ምንነት ስለሆነ የተፈጠረች አለ። መዝ ፻፴፮

ቅዱሳን አበው በዘመንና በቦታ ተለያየተው ቢኖሩም መንፈስቅዱስ ግን በአንድ ምስጢር አደራሽ ሰብስቦ በአንድ ልብ እንዲያስቡ በአንድ አፍ እንዲናገሩ አደረገ። ይሄም የተባለበት ምክንያት ቅዱስ ኤራቅሊስ «.....ከንጹሕ አፈር የተፈጠረች ድንግል.....» ብሎ ሲመሠክር ፤ ቅዱስ ቴዎዶጦስ ዘዕንቁራ ደግሞ እንዲህ በማለት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ይመሠክራል።

ወሰመያ ለእግዝትነ ማርያም ድንግል ወላዲቶ ወሊኦ እምከርሣ እንዘ ድንግል ይእቲ ወኢረኵሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ

በድንግልና ሳለች ከአርስዋ ተወልዶ ድንግል ማርያምን እናቴ አላት ከፈጠራትም ጀምሮ በምንም በምን አልረከሰችምና ሃይ አበ ፶፫፡ ፳፪ (53 ፥ 22)

ቅዱስ ቴዎዶጦስ «..ከፈጠራትም ጀምሮ በምንም በምን አልረከሰችምና...» ብሎ ለይቶ በመናገር በእናቷ ማሕፀን ከፈጠራት ጀምሮ ንጽሕት እንደሆነች መሠከረ እንጂ ከተወለደች ወይም ከተበሠረች ጀምሮ አላለም። ነገራቸነን ለማጉላት ሰው ተፈጠረ የሚባለው ሲፀነስ ነው ፤ ከእናቱ ማሕፀን ቆየቶ ወደዚህ አለም ሲመጣ ግን ተወለደ ነው የሚባለው። እንዴት ቢሉ እናትና አባት ወላጆች ሲሆኑ ነፍስና ሥጋን አዋሕዶ የሚፈጥር ግን እግዚአብሔር ስለሆነ። ኤር ፩፡ ፭ኽ (1 ፥ 5-6)

ደፋሮችና ሐሰተኞች ብቻቸውን ይቅሩ እንጂ እኛስ ቅዱሳን አባቶቻችን ይመሰክሩልናል።

ምሥጢረ ሥጋዌን አምልቶና አስፍቶ የተናገረው ንዑድ ክቡር ዮሐንስ ፤ አፈ ወርቅ በተባለው አንደበቱ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም እንዲህ ሲል ያመሠጥረዋል።

«..ከመ ገባሪ ጠቢብ ሶበ ይረክብ ግብሮ ዘይትጌበር ይገበር አምኔሁ ንዋየ ሠናየ ከመዝ እግዚእነ ሶበ ረከበ ሥጋሃ ቅዱሰ ለዛቲ ድንግል ወነፍሳ ቅድስተ ፈጠረ ሎቱ መቅደሰ ዘቦቱ ነፍሰ ፤

እንደ ብልሀ ሸክላ ሠሪ የሚሠራውን የለዘበ ጭቃ ባገኘ ጊዜ ከእርሱ መልካም ዕቃ እንደሚሠራ እን ደዚሁ ጌታችን የዚችን ድንግል ንጽሕት ሥጋዋን ነጽሕት ነፍስዋን ባገኘ ጊዜ ነፍስ ያለችውን ሥጋ ሊወሐደው ፈጠረ..» ሃይ አበ ም ፍኗ፡ ፲፬ (66 ፡14)

ይህ አባት የጥበቡ ስፋት የማይመረመረውን አምላክ በብልሀ ሸክላ ሰሪ ፤ ድንግልን በለዘበ ጭቃ ምሳሌ መሰለ። የለዘበ ማለት ያልገረበ ፤ያልደረቀ ፤ ለመሥራት የተመቸና የተዘጋጀ ፤ ገር ማለት ሲሆን ድንግልም በሐሩረ ኃጢት ሳትደርቅ ጥንቱን እርሱ ሊያደርገው ለወደደው የማዳን ሥራ የተመቸችና የተዘጋጀች ሁኖ ቢያገኛት ከእርስዋ ሰው ሆነ። የውርስ ኃጢአት በነፍሰም በሥጋም ሲሆን ሊቁ ግን ድንግል ከመርገመ ነፍሰ ከመርገመ ሥጋ ነጻ ሁና መፈጠርዋን ሲነግረን ንጽሕት ሥጋዋን ነጽሕት ነፍስዋን ባገኘ ጊዜ ብሎ አጉልቶ አምልቶ መሠከረ።

የኢትዮጵያው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በዚህ ምሥጢር ሲያብር ፤

አንጺሐ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ኃደረ ቃል ላዕሌሃ ፤ ድጓ ዘነሐሴ ኪዳ ምሕ
ሥጋዋን አንጽቶ እርስዋን ለይቶ አክበሮ አካላዊ ቃል ከርስዋ ተዋሐደ ፤ ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን በምሥጢር አበረው።

አእምሮ ለብዎ የተነሳቸው ደፋሮች ለስሕተታቸው ድጋፍ ያገኝን መስሏቸው ቅዱስ ያሬድ እንደዚህ ማለቱ ከብሥራተ መልአክ በኋላ መንጻቷን ሲናገር ነው ለማለት ይሞክራሉ ፤ አሁንም በይሆናል እንጂ አያስኬዳቸውም። ምክንያቱም ቅዱስ ያሬድ ኃይለ ቃልን ፤ ምስጢርን እንጂ የንባብ ቅደም ተከተል ላይ አይደለም የሚያተኩረው። ለምሳሌም ያህልም

1. *ከመ ይሥዓር ጣዖተ ፤ ወከመ ያብርህ ጽልመተ ፤ ዲበ ዕፀ ተሠቅለ ፤ በሠላሳ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ፤ ዘነበያት ሰበክዎ ወአስተርአየ ገሠደ ፤* ድጓ ዘዘመነ አስተርእዮ።

   ጣዖትን ይሸር ዘንድ ጨለማንም ያበራ ዘንድ (3) በእንጨት ተሠቀለ ፤ በሠላሳ ዓመቱም (2) በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፤ ነቢያት የተነበዩለት እርሱ(1) በግልጽ ታየ።

ከዚህ ላይ እንደሚታየው ቅደም ተከተሉን ያልጠበቀ መሆኑ ገልጽ ነው። በምሥጢር ግን ሊቁ ከልደት እስከ ሞት ያለውን የነገረ ደኅንትን ምሥጢር ባጭር ዐረፍተ ነገር ነገረን እንጂ ከተሠቀለ በኋላ ተጠመቀ ፤ ከተጠመቀም በኋላ ታየ ማለቱ እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽነው።

2. «*ዮም ንወድሳ ለማርያም.....ዶረቶ በከርሣ ወእቱኒ ቀደሳ.....*» የሚለውን ብንወስድ *ዶረቶ በከርሣ ወእቱኒ ቀደሳ ፤-* እርስዋ በማሕፀንዋ ተሸከመችው እርሱም ቀደሳት ንባቡን በቀጥታ ብንመለከተው እመቤታችን ጌታን ከጸነሰችው በኋላ እንደቀደሳት እንዳነጻት ነው የሚመስለው። ግን ነገሩ ፈጽሞ እንዲህ አለመሆኑ የታወቀ ቢሆንም ፤ እንዲያው ለዚሁ ብቻ «የድኃ አዛኝ ቅቤ አንቺች...» እንሁንላቸውና በቀጥታ እንደንባቡ ቢወሰድ ቀልጠው የሚቀሩት ያው ደፋሮቹ ናቸው። ምክንያቱም እነርሱ ከብሥራተ መልአክ በኋላ ነው ካሉ ፤ ከዚህ ደግሞ ከፀነሰችው በኋላ ቀደሳት ካለ ፤ ብሒላቸውን ያፈራርስባቸዋል። ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ ሊስማማቸው ስለማይችል ቢርቁት ይሻላቸዋል።

ቅዱስ ያሬድ ግን ድንግል ማደሪያውን ከጥንተ አብሶ ንጹሕ አድርጎ እንደፈጠራት ሲነግረን *አንጺሐ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ* ሥጋዋን አንጽቶ እርስዋን ለይቶ አክበሮ አለና ጥንቱን የተመረጠችበትን ፍጻሜ *ኃደረ ቃል ላዕሌሃ* አካላዊ ቃል ከርስዋ ተዋሐደ ካለ በኋላ ሊቁ....

ለልየ በእደየ ለሐኩዋ ለድንግል እንተ አምኔሃ ተሰባእኩ ይቤ እግዚአብሔር ፤ ድጓ ዘነሐ ኪዳ ም
ከእርስዋ ሰው የሆነኩባት ድንግልን እኔ ራሴ በእጄ ፈጠርኳት አለ እግዚአብሔር...» ሲል መንገድ ይዘጋባቸዋል። ስለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድ ሊስማማቸው ስለማይችል ቢርቁት ይሻላቸዋል ያልንው።

የሚገርመው እርሱ ራሱ ለብቻው ለእናትነት መረጦ ያዘጋጃትን እመቤት እንወደደ አድረጎ ቢፈጥራት ፈቃዱ የራሱ ነው። ለምን እንዲህ አድረጎ ፈጠራት ብሎ በመለኮትነቱ ስራ ቢገቡበት ጌታ አይወደም ፤

«*በከመ ፈቀደ ይገብር ወበከመ ሀለየ ይፈጽም* አንደወደደ ይሠራል እንደ አሰበም ይፈጽማል..» ይለዋልና።

ዳግመኛም ይህ ቀዱስ አባት ዮሐንስ አፈ ወርቅ አመቤታችንን ባመሰገነበት በሃያ ስድስትኛው ክፍል እን ዲህ ይላል። *ተፈሥሒ ኦ ማርያም* <u>*እንተ ብኪ ተበትከ ማዕሠረ ሔዋን ማሕመሚ*</u> *እንተ ገደፋ አግዚአብሔር ውስተ ደይን*።

እግዚአብሔር በሲኦል የጣላት <u>የሔዋን ጽኑ ፍዳ ባንቺ የጠፋ</u> ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ፤ ሃይ አበ ፷፭ ፡ ፴፮
<u>ክርስቲያኖች ሆይ ይሄን ምሥጢር እናስተውል</u> ፤- <u>ሔዋን</u> ያመጣቸው ፍዳ በሔዋን እና በልጆችዋ ቀረ እንጂ (በዘርዋ) ምንም ልጅዋ ብትሆንም ቅሉ በእመቤታችን ፈጽሞ የሌለ በመሆኑ <u>የሔዋን ጽኑ ፍዳ</u> ብሎ ባለቤትነትን ለሔዋን ሰጠ እንጂ የግድ በጉልበትና በድፍረት ድንግልን የፍዳ ተጋሪ አላደረጋትም። ለይቶም ሲናገር <u>ባንቺ የጠፋ</u> አለ እንጂ <u>ስለአንቺ የጠፋ/የጠፋልሽ</u> አላለም።

<u>ቅዱስ ያሬድ በምስጢር ሲያብር</u>

ይተፈሣሀ ልብኪ ኦ ድንግል ወይትሌዐል ቀርነኪ በክብር ሰማይ ዳግሚት <u>*ብኪ ደኅነ ዓለም*</u> *ወበወልደኪ ኮነ ሰላም* ፤ ድኅ ዘነሐ ኪዳ ም
ድንግል ሆይ ልቦናሽ ደስ ይሰኝ ፤ ስልጣንሽም በክብር ከፍ ከፍ ይበል ፤ ሁለተኛዋ ሰማይ ሆይ <u>ባንቺ ዓለም ዳነ ፤ በልጅሽም ዕርቅ ሆነ</u>። አለ ሉቃ ፩ ፵፯ ኽ፵፰ (1 ፡ 47-48) መዝ ፵፬ ፲፯ኽ፯ (44 ፡ 16-17) ኤፌ ፪፡ ፲፬ ኽ፲፯ (2 ፡ 14-17) ከእርስዋ በነሳው ሥጋ ነውና ዓለሙን ያዳነ <u>ባንቺ ዓለም ዳነ ፤ በልጅሽም ዕርቅ ሆነ</u> አለ።

<u>አባ ሕርያቆስ ስትፈጠር ጀምሮ የተጎናጸፈችውን ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ በአንክሮ ሲገልጽ ፤</u>

በአማን ነጸረ አግዚአብሔር አብ አምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኩሉ አጽናፍ ፤ አስተንፈሰ ወአጼነው <u>*ወኢረከበ ዘከማኪ ወሠምረ መዓዛ ዚአኪ ወአፍቀረ ሰንኪ*</u> *ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር ፤*

እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ሆኖ ምሥራቁንና ምዕራቡን ፤ ሰሜኑና ደቡቡን ፤ የዓለሙን ዳርቻ ሁሉ በእውነት ተመለከተ ተነፈሰ አሻተተ <u>እንዳንቺ ያለ አላገኘም</u>። የአንቺን መዓዛ ወደደ ደም ግባትሽን ወደደ የሚወደውን ልጁን ወደ አንቺ ሰደደ። ቅዳ ማር ፤ መዝ ፵፬ ፲፻፭ (44 ፡ 10-11)

በአራቱ ማዕዘን ያለው ሁሉ በአዳም በደል የተያዘ ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ማርያም ግን ከፍጥረቱ ሁሉ ተለይታ ንጹሕ ሁና ስለተፈጠረች ግልጽ በሆነ ቃል <u>እንዳንቺ ያለ አላገኘም</u> አለ እንጂ እንደሰው የውርስ ኃጢአት ቢኖርባት ኖሮ እንዲህ ለይቶ ባልተነገረ ነበር።

በደሙ የከበራችሁ ክርስቲያኖች ሆይ ጠቅለል ባለ መልኩ ድንግል እሰከ አሁን በተመለከትነው ሁኔታ ለእናትነት ተመርጣ ቀነ ቀጠሮው ሲደርስ በማይመረመር ምሥጢር ጌታዋን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደችው። ገላ ፬፡ ፬፳፮ ፴፫ ዓመት ከሦስት ወር አብራው ኖረች ፤ አስቀድሞ በዓረጋዊው ስምዖን እን ደተነገራት በሕማሙና በሥቅለቱ በሞቱና ወደመቃብር በመውረዱ የኃዘን ሰይፍ በልቧ አለፈ። ሉቃ ፪ ፡ ፴፭ ኽ፴፮ (2 ፡ 35-36)

ዓለሙ በዳነባት (ዕለተ ዓርብ) በዚያች ቀንም በነቢዩ በዳዊት *ወናሁ ኢሎፍሊ ወጢሮስ ወሕዝበ ኢትዮጵያ አለ ተወልዱ በሀየ ፤ አምኑ ጽዮን ይብል ሰብአ* ፤ እነሆ የኢሎፍሊና የጢሮስ የኢትዮጵያም ሕዝብ በዚያም የተወለዱ ፤ ሰው እናታችን ጽዮን ይላል..» መዝ ፹፯፡ ፭ ኽ፮ (86 ፡ 5-6) ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ በዮሐንስ አማካኝነት እርስዋን ለእኛ እናት እኛን ለእርስዋ ለጆች አድረጎ አረካከበን ዮሐ ፲፱፡ ፳፭ ፴፩ (19 ፡ 25-31)

ከዚያም ጌዜ ጀምሮ ፤ «..*ይእቲ ማርያም አምኑ ወእሙ ለእግዚእነ ሰአሊ በእንቲአነ* ፤

እርስዋ እመቤታችን እናታችን ናት የጌታችንም እናት ናት..» ብለን በመመሥከር ከክንፈ ረድኤትዋ ሥር ሆነን *ሰአለ ለእንቲአሃ* **ለምኝልን** እያልን የእናትነትዋን ፍቅር እየተመገብን እንኖራለን።

ዕረፍተ ሶልያና ፤

አሜሪካ የከንሳስ ደብረማህል መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን «**እመቤታችን ቅድስት ማርያም የሞተችው የውርስ ኃጢአት ስላለባት ነው»** ብለው አባ ሲኖዳ መሥክረውልናል የሚል ባወጡት መግለጫ አስቀምጠዋል።

በመግቢያው እንደተነገረው አባ ሲኖዳ ያመኑበትንና የመሰላቸውን መናገር መብታቸው ነው። በኦትዮጵያውያን ዘንድ ግን ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንቱም እናት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ብላ አታስተምርምና ስለምን ? ቢሉ ነገሩ ከእውነት የራቀ ብቻ ሳይሆን በነገረ ደኅንት (በሞተ ወልደ እግዚአብሔር) ታላቅ ተፋልሶ የሚያመጣ ስለሆነ ነው ፤ ይሄንንም እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

1.ኛ **እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም** ከጥንተ አብሶ (የአዳም በደል) ነጻ ሁና እንደተፈጠረች በቅዱሳት መጻሕፍት ምሥክርነት ሰፋ ባለ መልኩ ተረድተናል። አሁን ደግሞ እንኳንስ የእርስዋ ከጥንተ አብሶ ነጻ ሁና የተፈጠረችው ሞት ይቅርና የእኛ ሞት እንኳ ከላይ በተነገረው መልክ አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን አባባላቸውም ትልቅ ስህተት እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል።

2.ኛ **የውርስ ኃጢአት ነጻነት ፤** **«...ወዘኒ ሞተ ምዕረ ሞተ ወበሞቱ ሠዐራ ለኃጢአት ፤ የሞተውም እንድ ጊዜ ሞተ በሞቱም ታጢአትን ሻራት..»** ሮሜ ፮ ፲፩ (6 ፥ 10-11) እንዲል ሎቱ ስብሐት (ምስጋና ይደርሰው) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለአዳም (ስለእኛ) በደል ሲል ራሱን መሥዋዕት በማድረግ የእኛን ሞት ሙቶ በሞቱ ሞትን ገድሎ በደሙ ፈሳሽነት እኛን ከውርስ ኃጢአት ነጻ አድርጎ የቀደመ ልጅነታችንን ስለመለሰልን ከዕለተ ዓርብ ጀምሮ በስሙ የምናምን ፤ ከጎኑ በወጣው ማየ ገቦ የምንጠመቅ ፤ ቅዱስ ሥጋውን ከቡር ደሙን የምንቀበል ሁሉ የምሥራች መርገም ተደመሰሶልን ቍራኝነት ጠፍቶልን ከውርስ ኃጢአት ነጻ ነን። ይሄን ያልተረዳ ማንኛውም ክርስቲያን (መሪም ሆነ ተመሪ) ካለ ገና ክርስትናው አልገባውም ማለት ነው። አልመሰጦ ፬፡ ፭። ቆሮ ፲፭፡ ፪። ቆላ ፪፡ ፲፬፣፳፯። ዕብ ፪ ፡ ፲፬፣፳፭።

3.ኛ **የክርስቲያኖች ሞት** ፤ ከዚህም በኋላ የምንሞተው ሞትም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞትን ሥልጣን ሽሮ የእኛ ሞት በቍራኝነት ሳይሆን በእደ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ለእኛ አብነት ለመሆን ክብርት ነፍሱን «አባት ሆይ ነፈሴን አደራ እሰጣለሁ» ሉቃ ፳፫፡ ፵፮፣፵፮ ብሎ የሞትን መን ገድ ስለቀየረው እኛም «..**ወእመሰኬ ተመሰልናሁ በሞቱ ንትመሰሎ በሕይወቱሂ ፤ በሞቱ ከመሰልነው በሕይወቱም እንመስለዋለን..»** ሮሜ ፮፡ ፭ እንዲል ለዘለዓለም ሕይወት የርሱን ሞት አብነት አድረገን እንሞታለን በትንሳኤውም እንነሳለን እንጂ በጌጋየ አዳም የምንያዝና የምንሞት አይደለንም። ይህንንም ሊቁ ቄርሎስ (እነ አባ ሲኖዳ ከሰሙት)
«..ወአሜሃ በውእቱ መዋዕል ኮና ነፍሳት ሶበ ይወፅኣ እምሥጋ ሰብእ ይወርዳ መትሕተ ምድር ወይተፈነዋ ውስተ ገሃነም እስከ ይመልዓ አብያተ ሞት። ወሶበ መጠወ እግዚእነ ክርስቶስ መንፈሶ ውስተ እደ እግዚአብሔር አቡሁ አስተዳለወ ለነ ፈኖተ ሐዲስ ውስተ ሰማያት ወኢነሐውር እንከ ውስተ ገሃነም አላ ንተልዎ ለዘፈጠረነ ወከመዝ ነሜጡ ነፍሳቲነ ውስተ እዴሁ።

ያን ጊዜ በዚያ ወራት ነፍሳት ከሥጋቸው በተለዩ ጊዜ ከምድር በታች ወደ ሲኦል ይወርዱ ነበር ፤ የሞት ቤቶችም እስኪ ሞሉ ድረስ ወደ ገሃነም ይሄዱ ነበር ጌታችን ክርስቶስ በአባቱ ሥልጣን ነፍሱን ከሥጋው በለየ ጊዜ ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት **አዲስ መንገድ አዘገጀልን** ፤እንግዲ ወዲህ ወደ ገሃነም እንሄድም ፈጣሪያችንን እንከተለዋለን እንጂ በስልጣኑ ነፍሱን ከሥጋው እንደለየ **የእኛም ነፍስ በእርሱ ሥልጣን ትለያለች**....»። ሃይ አበ ፹፡ ፲፯ (80 ፥ 17) ሲል ያብራራዋል።

4.ኛ የድንግል ሞት ፤ ጥንት አብሶ ከጠፋ ፤ ቍራኝነት ከቀረ ፤ ሞት ከተሻረ ከ፲፭ (15) ዓመት በኋላ ነው። ከላይ ዘርዘር ባለ መልኩ እንደተመለከትነው ከሆነ ፤ ታዲያ እንዴት ተብሎ ነው ሞትን የሻረውን አምላክ እናት የአዳም በደል ስለለባት ነው የሞተቸው ተብሎ እንኳዋን ለመናገር ሊታሰብስ

የሚገባው? ኧረ እናስተውል ወገኖች። ይሄማ ለኛ ብሎ የሞተውን ሞት ክንቱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሊወገዝ የሚገባው ተላቅ ስተት ነው። ይህን እንተወውና ወደ እውነቱ እናምራ።

5.ኛ **የድንግል ሞት ምሠጢረ ሥጋዌን ያጎለዋል ነው**። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሲሆን ፈጹም ሰውም መሆኑን ለማጠየቅ በሥጋ የወለደችው ምድራዊት እናቱ መሞት ነበረባት። ድንግል ባትሞትማ ኑሮ በየዘመኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሱ ፤ ኃይል አርያማዊት ናት ለሚሉ ፤ አምላክ የነሳው ሥጋ ከሰማይ ነው ለሚሉ (አፍትኪስ) ፤ ሥጋ በቅድምና ነበረ ለሚሉ (ንስጥሮስ) ፤ ምትሐት ነው ለሚሉ (መንኪዮን) ፤ መናፍቃን ምስጢር በቀናላቸው ነገር በደላደለላቸው ነበር።

6.ኛ **ጌታ በፈታሒነቱ አድልዎ እንደሌለበት ለማጠየቅ** ፤ በእናት ላይ «..ትሙት በቃ» ተብሎ ባይበየን ም ቅሉ ፤ እርሱ የእርስዋን ሥጋ ለብሶ የሞተውን ሞት እናቱም ሥጋ ለባሽ ስለሆነች መሞት ነበረባት። ለዚህም ነው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ

እንበይነዝ አእምሩ በውስተ ፍትሀ ከመ ኢያደሉ ትዋአም ሞተ እሙ ወእመ ኩሉ አዘዘ ወልድ በርቱዕ ቃሉ።
ስለዚህ በፍርድ እንደማያዳላ እወቁ እናቱ (በስጋ) ፤ የሁሉም እናት (በቃልኪዳን) ሞትን ትቀመስ ዘንድ ወልድ (ልጅዋ) በማያዳላ ቃሉ አዘዘ..» በማለት ያመሠጠረው። ድጓ ዘነሐሴ ኪዳ ምሕ ።

7. **በእግዚአብሔር (በልጅዋ) ጥሪ** ፤ እመቤታችን ከጌታ ሞት በኋላ በዮሐንስ ቤት አሥራ አምስት ዓመት ቆይታ መለ እድሜዋ ፷፬ (64) ሲሆናት ጥር ፳፩ ፵፱ ዓም እሁድ ቀን አርፋለች። ይሄውም
«...ተንስኢ ወንኢ ቅርብትየ እንቲአየ ሠናይት ርገብየ እስመ ናሁ ክረምት ኃለፈ.....መኃ ፪፡ ፲፫፮
አቅራቢያዬ መልካሟ ርግቤ የኔ ሆይ ነዪ ክረምቱ (የመከራው ዘመን) አልፏልና...» ብሎ ልጅዋ ባቀረበለት ጥሪ መሠረት ነው። ይሄንንም ጥሪ ቅዱስ ያሬድ

ሰላም ለኪ ማርያም እመ አምላክ ወልድኪ ይጼውዐኪ ውስተ ሕይወት ወመንግሥተ ክብር ፤
የአምላክ እናት ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ፤ ወደ ሕይወትና ሉዐላዊ ክብር ልጅሽ ይጠራሻል። ሲል ይገልጸዋል ድጓ ዘነሀሴ ኪዳ ምህ። ። ቀጠል አድርጎ ይህ ሊቅ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመቸው እናቱ ናትና በዕረፍትዋ ጊዜ ክብርት ነፍስዋን ለመውሰድ እንደወረደ ሲነግረን ፤..

«...ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና ወረደ ወልድ እምዲበ ልዕልና ጠሊሳነ ንግሥ ሶቤሃ ከደና ፤ **ድጓ ዘአስ ማር። በሶልያና (ማርያም) ዕረፍት ጊዜ ወልድ ከለዕልናው ወረደ የንግሥና መጎናጸፊያም አለበሳት..» ይላል።**

ታሪኩ ሰፋ ያለ ስለሆነ ባጭሩ እንዲህ በእኛ አንደበት ሊገለጽ በማይችል ክብር ነፍስዋን ከእርሱ ጋር አሳረገ ፤ ሥጋዋን በጌቴሴማኒ ሐዋርያት እንቀብራለን ሲሉ ፤ የልጅዋ ጠላቶች አይሁድ አናስቀብርም በለው ሑከት ስላነሱ መላኩ ወስዶ በዕፀ ህይወት ሥር አኖራት። ሐዋርያት ሱባዔ ገብተው ፈጣሪያቸውን ጠየቁ ነሐሴ ፲፬ አምጠዉ ሰጣቸውና ቀበርዋት በ፲፮ ተነስታ አርጋለች።

ማጠቃለያ ፤-

በቅዱሳት መጻሐፍት ዋቢነት ፤ በነቢያት ትንቢት ፤ በሐዋርያት ስብከት ፤ በሊቃውንት ትምህርት ፤ እናት ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም በደል ያላገኛት ፤ ዘለዓለማዊት ድንግል ፤ በአማላጅነትዋ ይቅርታ የምታሰጥ ፤ ንጽሕት ክብርት ቡርክት ቅድስት የዓለም መድኃኒት እናት ናት ብላ ታምናለች ታስተመራለች ፤ ልደትዋን ዕረፍትዋን ዕርገትዋን ታከብራለች። ከዚህ ውጭ የሆኑቱን ደግሞ.... ፤

« አመቦ ዘይብል ከመ ድንግል ቅድስት ይእቲ ኃይል አርያማዊት ውጉዘ ለይኩን።
ቅድስት ድንግል ሰማያዊት ናት የሚል ቢኖር ወጉዝ ይሁን ፤ ብላ ታወግዘለች።

ትምህርቷን የሚሰሙትን ቃልዋን የሚቀበሉትን ደግሞ ፤-

ወዘሰ የአምን በጽድቅ ከመ ድንግል ቅድስት ማርያም እምዘርዓ ዳዊት ወይሁዳ ወአብርሃም ይእቲ በከመ ጽሑፍ ውሰተ ቅዱሳት መጻሕፍት ፍቱሕ ውእቱ።

<u>በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ ቅድስት ድንግል ማርያም ከዳዊት ከይሁዳ ከአብርሃም ዘር እንደሆነች በአውነት የሚያምን ከግዝት የተፈታ ይሁን»</u> ብለ ትባርከቸዋለች ሃይ አበ ፻፳፫ ፡ ፵ (123 ፡ 8)

እኛም የቅድስት ድንግል የቃልኪዳን ልጆችዋ በነቢዩ ዳዊት *ወይዘክሩ ሰመኪ በኩሉ ትውልደ ትውልድ* ፤ <u>ስምሽን ለልጅ ልጅ የሳስባሉ</u> መዝ ፵፬፡ ፲፯ (44 ፡17) ትብሎ እንደተነገረ አስክ መጨረሻው እንዲህ እናስተምራለን እንዲህ እንመሠክራለን።

የጌታችን መደኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት ፤ የእናታችን የንጽሕተ ነጹሓን ድንግል ማርያም አማለጅነት አይለየን።

ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ለመላው ዓለም ሰላም ፤ ለቤተክርስቲያናችን አንድነት ያድልልን።
አሜን።

መሪ-ጌታ ገብስላሴ ዘተዋሕዶ